## 8ኛ ትምህርት

*ከነሐሴ 7 — 13* *Aug 13 - 19*

# የየሱስ ርኅራኄ

### ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ 2ነገሥ. 13:23፣ ዘፀ. 2:23—25፣ ሉቃስ 7:11—16፣ 1ዮሐ. 3:17፣ ዮሐ. 11:35፣ ሮሜ. 12:15፣ 2ቆሮ. 1:3-4።

**የሳምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡-** “የሱስም ከጀልባው ሲወርድ ብዙ ሕዝብ አይቶ ራራላቸው፤ ተኞቻቸውንም ፈወሰላቸው” (ማቴ. 14:14)።

ገና የ17 ዓመት ቀንበጥ ናት። ይህች ወጣት ብዙዎች በእርሷ የዕድሜ ክልል ያሉ እኩዮቿ ሊገጥማቸው ከሚችል ብርቱ ፈተናና የልብ መሰበር ጋር ስትታገል ከርማለች። በስተመጨረሻ ግን አልሆነላትም። የከፋው ደረሰና ተሸነፈች። አዎ፤ በራሷ ውሳኔ እስትንፋሷን ገታች፣ የልብ ትርታዋንም አቆመች። ይህን ተከትሎ በወላጆች ሊደርስ የሚችለውን ሰቆቃ ከቶ ማን ሊገምት ይችል ይሆን?

የቤተ ክርስቲያናቸው መጋቢ የተሰማቸውን ጥልቅ ሐዘን ለመግለጽ ብሎም ለማጽናናት በሐዘንተኞች ቤት ተገኙ። ወላጆች ባሉበት ሳሎን ቤት ቁጭ አሉ። ሆኖም ካንደበታቸው አንድም ቃል ሳይወጣ ረዘም ላሉ ደቂቃዎች በዝምታ ቆዩ። በእርግጥ ፓስተሩ በቤተሰቡ የሐዘን ድባብ ሰምጠው ነበር። ከዚያም ሳግ ያዛቸው። ከልብ ተንሰቀሰቁ፡ ፡ እንባቸው ዐይኖቻቸውን አርጥቦ ቁልቁል ኮለል ቢልም ሊያቆሙት ግን አልተቻላቸውም። በዚህ ሁኔታ ጥቂት ቆዩ። በመጨረሻ አንዲትም ቃል ትንፍሽ ሳይሉ ወጥተው ሄዱ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ወላጅ አባት ከፓስተሩ ጋር ተገናኙ። በሐዘናቸው ለመካፈል ቤታቸው የመጡ ዕለት ስላደረጉት የተሰማቸውን አድናቆት ገለጹላቸው። በወቅቱ እርሳቸውም ሆኑ ባለቤታቸው አጥብቀው ይሹ የነበረው በሐዘናቸው መገኘታቸውን ብቻ እንጂ አንድም የማጽናኛ ቃል ለመስማትም ሆነ የተስፋ መልእክት ወይም የምክር አገልግሎት ለማድመጥ ዝግጁ እንዳልነበሩ ነገሯቸው። “ፓስተር፡ በልጃችን ሕልፈት የሐዘናችን ተካፋይ የሆኑበት ያ ሁናቴ በእርግጥ ለእኔና ለባለቤቴ ምን ያህል ትርጉም እንዳለው ልነግርዎ አልችልም።” በሐዘን ልባቸው የተሰበረ ወገኖችን በመጎብኘት የክፉ ቀናቸው ተካፋይ መሆን መሃላቸው በ “መደባለቅ” ያን ቀድሞ የነበረ ግንኙነት ወደ አዲስና የተሻሻለ ደረጃ ማሳደግ ነው።

የሐዘን ተካፋይ መሆንና ማጽናናት የሱስ ወደ ሰዎች የደረሰበት እጅግ ወሳኝና አስፈላጊ መንገድ ነው።

*እሑድ ነሐሴ 8* *Aug 14*

## ሐዘን የተቀመጡትን መጎብኘት

እጅግ ግዙፉ ዩኒቨርስ አስፈሪ ገጽታ የተላበሰ ሊሆን ይችላል። የህዋን ስፋት፣ ቀዝቃዛነትና ግዝፈት ስናስብ ኢምንት፣ ከንቱና ባዶ እንደሆን ሊሰማን ይችላል። የዘመናችን ሳይንስ ግስጋሴና ምጥቀት ይህ ፍርሃት ይበልጥ እንዲጨምር መንስኤ የሆነ ይመስላል። በቅርቡ የተሠሩ ግዙፎቹ ህዋን አጉልተው የሚያሳዩ መነጽሮች ዩኒቨርስ እኛ ከምናስበውና ከምናልመው በላይ እጅግ ግዙፍና ውስብስብ መሆኑን ይፋ እያደረጉ ይገኛሉ። በዚህ ላይ ቢፈልጉ--የፈጣሪ የእጆቹ ሥራ ውጤት ናቸው የሚለውን አስተሳሰብ በመቃወም ዝና ያተረፈውን የዳርዊንን ከንቱ ሙግት ያክሉበት። ሰዎች ቁልቁል ከሚጫን የተስፋ መቁረጥ ስሜት ጋር በይፋ እየታገሉና እየተፋለሙ--ስለ እኛ ፍጹም ግዴለሽ የሚመስለው ግዙፉ ሕዋ ግን እነሆ ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ ተንጣሎ ይታያል። በእርግጥ መጽሐፍ ቅዱስ እኛ በፍጥረት ውስጥ ስላለን ስፍራ ለየት ያለ ምልከታ ይሰጠናል።

እግዚአብሔር ስለ ወደቁትና ከእርሱ ስለ ተነጠሉት የምድር ፍጥረታት ስላው ርኅራኄ የሚከተሉት ጥቅሶች ምን ያስተምሩናል?

መሳ .2:16—18

______________________________________________________________________________

2ነገሥ. 13:23

______________________________________________________________________________

ኢሳ. 54:7, 8, 10

____________________________________________________________________________

እግዚአብሔር የሱስ በአዲስ ኪዳን ከተገለጠበት ለየት ያለ መንገድ በተቃራኒ እንደ ጥብቅ፣ ኃይለኛ፣ ቁጡ፣ ይቅር የማይል፣ ርኅራኄ የሌለው አምላክ ተደርጎ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ቢሳልም--እነዚህ ከላይ የቀረቡት፤ እግዚአብሔር ለሰብዓዊው ፍጡር ያለውን ርኅራኄ ከሚያሳዩ ከብዙዎቹ የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች ጥቂቶቹ ናቸው፡ ፡

እግዚአብሔር በሥቃይ ውስጥ ለሚገኙ ወገኖች ምን ያህል ግድ እንደሚለው ዘፀ. 2:23-25 ምን ይለናል?

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---

እግዚአብሔር ለሕዝቡ ርኅሩኅና መሐሪ ነው (ያዕ. 5፡11)። ይህ ደግሞ የመላው መጽሐፍ ቅዱስ ገጾች ርዕሰ ጉዳይ ነው።

“ሐዘናችን ብቻ ሳይሆን አሳዛኝ አነጋገራችንም ጭምር ያን አፍቃሪ ልቡን ይነካዋል... ሰላማችንን ሊነካ የሚችል ከእርሱ ዕይታ የሚሰወር ኢምንት ነገር እንኳ ሊኖር አይችልምና. . . የሰማዩ አባታችን ሳያየው ከታናናሾቹ ልጆቹ በአንዳቸው ላይ ሊደርስድ የሚችል አደጋም ሆነ አሳዛኝ ሁኔታ የለም።”–Ellen G. White, Steps to Christ, p. 100.

በሚኖሩበት ማኅበረሰብ መሃል የደረሰ ሐዘን አለ? እግዚአብሔር የእነዚህን በሐዘን የተጎዱ ወገኖች ስሜት እንዲጋሩና እንዲያጽናኑአቸው እንዴት ሊጠቀምብዎ ይችላል?

## ርኅሩኅ አዳኛችን

የሱስ ከሕዝቡ ጋር ተቀላቅሎ የኖረበት ያ ምድራዊ አገልግሎቱ ለሰዎች ያለውን ሐዘኔታና ርኅራኄ የሚገልጽበትን መንገድ ከፍቶለት ነበር። "የሱስም ከጀልባው ሲወርድ ብዙ ሕዝብ አይቶ ራራላቸው፤ ሕመምተኞቻቸውንም ፈወሰላቸው" (Matt. 14:14)።

እነዚህን ጥቅሶች ያንብቡ፡--ማቴ. 9:35-36፣ ሉቃስ 7:11-16። ጥቅሶቹ እውነተኛ ሐዘኔታና ርኅራኄ ስለሚገለጹባቸው መንገዶች ምን ያስተምሩናል?

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

ሐዘኔታ በመባል የሚታወቀው ቃል ሌላ ተመሳሳይ ፍቺ ወዳለው ሀረግ ሊወሰደን ይችላል--የሰውን ችግር እንደ ራስ ማየት ወደሚል። ይህ የሰውን ችግር እንደ ራስ ማየት--ሰዎችን የመረዳት ወይም የሌሎችን ስሜት የመጋራት ችሎታ ነው።

ሐዘንና ርኅራኄ ማሳየት--የሌሎችን ሥቃይና እንግልት የምናስተውል ብቻ ሳንሆን ከሥቃያቸው እንዲያገግሙ ያለንን ተደራሽነት ያሳያል።

ምናልባት እንደ ቤት ቃጠሎና ሞት ያሉ አሳዛኝ ክስተቶች የማኅበረሰብዎ አካል በሆኑ ወገኖች ላይ መድረሱን ሲሰሙ ምላሽዎ ምን ሊመስል ይችላል? "እንዴት ያለ አሳዛኝ ክስተት ነው!" ብለው እንደ ማንም አጉተምትመው ያልፉታል? ወይስ የሚሰማዎ የሐዘን መጠን እግሮችዎ ወደ ተጎጂ ቤተሰቦች እንዲያመሩ ያደርጋሉ? እውነተኛ የሐዘኔታና የርኅራኄ ስሜት ተጎጂዎችን እንድናጽናና ብሎም ባልንጀሮቻችንን በተጨባጭ መንገድ--በንቃት እንድናገለግል ኃይል ይሆነናል። የሐዘን መግለጫ ፖስት ካርድ በመላክ ወይም በአካል ተገኝቶ ጥልቅ ሐዘንን መግለጽና አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ የሚተገበር የፍቅር ድርጊት--የእውነተኛ ርኅራኄ ግልጽ ውጤት ነው።

እንደ መታደል ሆኖ ብዙ ሰዎችን ጨምሮ የዕርዳታ ድርጅቶች ለታላላቅ ውድመቶች አፋጣኝ ምላሽ የመስጠት ሥራ ይሠራሉ። ይህ በእንዲህ እንዳለ በብዙ ችግር ውስጥ ለሚገኘው አጠገባችን ላለ ወገን መስጠት የሚኖርብንን ትኩረት ስንነፍግ እንስተዋላለን። የሱስ ሐዘኔታ ማሳየት ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ሐዘኔታውን ከፍ ወዳለው ደረጃ ማለትም ወደ ርኅራኄ አሳድጎት ነበር። እኛም እርሱ ያደረገውን እናደርግ ዘንድ በእርግጠኝነት ተጠርተናል። ማንኛውም ሰው ሌላው ተጎሳቁሎ ሲመለከት የሐዘኔታ ስሜት ሊሰማው ይችላል። ጥያቄው--የሐዘኔታው ስሜት ወደ ምን ዓይነት ተግባራዊ እንቅስቃሴ መራን? የሚል ይሆናል።

ባል ቁርሱን እየበላ ሚስት ደግሞ በሌላ አገር ስለ ተከሰተ አንድ አሳዛኝ ውድመት በጋዜጣ ላይ የተዘገበውን ዜና እያነበበችለት ነበር። ባልና ሚስት ስለ ደረሰው ጉዳት ስፋትና ጥልቀት በመጠኑ ከተነጋገሩ በኋላ ባል የወሬአቸውን ርዕስ በመቀየር የከተማቸው የእግር ኳስ ቡድን ከአንድ ቀን በፊት ባደረገው ግጥሚያ ተፋላሚውን አሸንፎ እንደሆነ ጠየቀ። እኛ ሁላችን ከዚህ ተመሳሳይ በሆነ ክስተት ጥፋተኞች ሆነን የምንገኘው እንዴት ነው? ይልቁንም እጅግ አነስተኛም ቢሆን አንድ ነገር እንኳ የማናደርገው ለምን ይሆን?

# የጉዳተኛውን ችግር እንደ ራስ ማየት

እነዚህን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ቆለ. 3:12፣ 1ጴጥ. 3:8፣ 1ዮሐ. 3:17። ጥቅሶቹ ምን እያሉን ነው? ይህን ርኅራኄ በህይወታችን ገልጠን ማሳየት የምንችለው እንዴት ነው?

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---

ርኅራኄ የሌሎችን ችግርና *ሥቃይ መጋራት* የሚል አንደምታ አለው። እኛ ሁላችን ችግርና መከራን ስለምናውቅ የሌሎችን *ሥቃይ*ና አሰቸጋሪ ሁኔታ ለማስተዋል አንቸገርም። ችግር ሲደርስብን የሌሎችን ሐዘኔታና ርኅራኄ እንደምንናፍቅ ሁሉ ለሌሎችም ተመሳሳይ ማድረግ ይጠበቅብናል።

የደጉን ሳምራዊ ታሪክ ቀደም ባለው ትምህርታችን ተመልክተን ነበር። የሱስ ለዚህ ደግ ሳምራዊ ምሳሌነት አጽንኦት በመስጠት እንዲህ ሲል ተናግሮአል "አንድ ሳምራዊ ግን እግረ መንገዱን ሲሄድ ሰውየው ወዳለበት ቦታ ደረሰ፤ ባየውም ጊዜ አዘነለት" (ሉቃስ 10:33)። የሳምራዊው መንገደኛ ሐዘኔታ ወይም ርኅራኄ ጉዳት ለደረሰበት ሰው እርዳታ እንዲያደርግ ገፋፍቶታል። ካህኑና ሌዋዊው "ይህን ሰው ብረዳው ምን እጠቀማለሁ?" ብለው እንዳሰቡ ሲገመት፤ ሌዋዊው ግን "ይህን ሰው ባልረዳው ምን ይደርስበት ይሆን?" በማለት ራሱን ሳይጠይቅ እንዳልቀረ ይታመናል። በታሪኩ ሳምራዊው የጉዳት ሰለባው ከሚገኝበት ትክክለኛ ገጽታ አኳያ ማድረግ የነበረበትን ከራስ ወዳድነት የራቀ ርምጃ ወሰደ። ለማያውቀው ባይተዋር ሰው ሲል ደኅንነቱንም ሆነ ንብረቱን አስጊ ሁኔታ ላይ ጣለ። በሌላ አነጋገር-- ክርስትና አንዳንዴ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ አስጊ ሁናቴዎችን ከመጋፈጥ አልፎ ዋጋ ሊያስከፍለን ይችላል።

የጠፋውን ልጅ ታሪክ ከዚህ ተምሳሌታዊ መልእክት አወቃቀር አኳያ ለመመልከት ይሞክሩ (ሉቃስ 15:20-23)። አባት በቤተሰባቸው መሃል ከነቀፌታና ከትችት በዘለለ ጠብና ሁከት ሊያስከትል የሚችል ምን ዓይነት ውሳኔ አሳለፉ? ርኅራኄን የሚገልጠው እቅፍ፣ የማን ልጅ መሆኑን የሚያሳየው ምርጥ አለባበስ፣ የመታመን ተምሳሌት የሆነው የጣት ቀለበት፣ የነጻነት ምልክቱ የእግር ጫማ እንዲሁም ግብዣና ድግሱ አባት የጠፋውን ልጃቸውን ወደ ቀድሞ ለመመለስ ሲሉ ራስ ወዳድ ባልሆነ ፍቅር ያላቸውን ሁሉ መሥዋዕት አድርገው ለመስጠት ምን ያህል ደስተኛ እንደሆኑ ያሳያል። በታሪኩ የጠፋው ልጅ የተላበሰው አባካኝና ከንቱ ባህሪ አስቀድሞውኑ ሊሄድበት ይችል የነበረውን መንገድ አመላካች ነበር። ሆኖም እዚህ ላይ ቆም ተብሎ ነገሩን--የጠፋው ልጅ ወደ ቤቱ ሲመለስ ካገኘው ምላሽ አኳያ ለማጤን ሲሞከር--በታሪኩ አባት የነበራቸውን ክብር ወደ ጎን በማለትና ደክመው ያፈሩትን ጥሪት እምብዛም ኃላፊነት በማይሰማው መልኩ ለአባካኙ ልጃቸው አውለዋል የሚል አስተያየት ሊሰነዘር ይችላል። አባት--በታላቁ ልጃቸው ዐይን አባካኝና ራሳቸውን መቆጣጠር የተሳናቸው መሆናቸውን የሚገልጥ ግዴለሽ ውሳኔ ወስነዋል። የአባት ርኅሩኅ ልብ ቤተሰቡን ያለ ጥሪት እንዳያስቀር ስጋት በገባው፣ በንስሐ በተመለሰው ልጅ ዐይን--አሁንም አባት እያባከኑ ነው።

እንዲህ ያለው የአዘኔታና የርኅራኄ ደረጃ ራስን አሳልፎ እስከ መስጠት የሚደርስ ውሳኔን ያካትታል። በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ወድቆ የነበረውን ተጎጂ በሁለት እግሮቹ ለማቆም የምንወስነውን ውሳኔ ተከትሎ የምንጋፈጣቸው አስጊ መሰናክሎች ለአደጋ ተጋላጭ ሊያደርጉን ይችላሉ። በአጭሩ--እወነተኛ አዘኔታና ርኅራኄ ዋጋ ሊያስከፍል ይችላል።

*ረቡዕ ነሐሴ 11* *Aug 17*

# የሱስ እንባውን አፈሰሰ

"ኢየሱስም እንባውን አፈሰሰ" (ዮሐ. 11:35)። ስለ የሱስ ሰብዓዊነት ለማሳት ሳይሆን ነገር ግን ያ ስብዕና ምን ያህል የሌሎችን ሥቃይ እስከ መጋራት እንደ ተሳሰረ ጥቅሱ ምን ይነግረናል? በተጨማሪ ሮሜ. 12:15 ይመልከቱ።

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
---

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
---

የሱስ ያሳየውን ርኅራኄ፣ የሰውን ችግር እንደ ራስ የማየት ሁኔታና ሐዘኔታ በዮሐ. 11:35 እንመለከታለን። በወቅቱ ምንም እንኳ የሱስ ሞቶ የነበረውን አልዓዛር ሊያስነሳው የነበረ ቢሆንም--እጅግ ቅርቡ የነበረው የዚህ ቤተሰብ ዋይታና ሰቆቃ አካሉንም ሆነ መንፈሱን አውኮት ነበር።

በእርግጥ የሱስ ያለቀሰው ውድ የነበረው ወዳጁ በመሞቱ ብቻ አልነበረም። ይልቁንም ኃጢአት በመላው ሰብዓዊው ፍጡር ላይ ያደረሰውን መጠነ ሰፊ ውድመትና ጥፋት በመመልከቱ ጭምር እንጂ።

"የሱስ ያለፉትን ዘመናት ሐዘንና ሰቆቃ ተሸክሞ ነበር። የእግዚአብሔርን ሕግ በመተላለፍ ምክንያት የሚደርሰው አሰቃቂ ውጤት ታይቶታል። በዓለም ታሪክ ከአቤል ሞት ጀምሮ በክፉና በደግ መካከል የተቀሰቀሰው ጦርነት አለመብረዱን ተመለከተ። ወደፊት የሚመጣውን ጊዜ ሲመለከት የሰብአዊ ዘር ዕጣ ፈንታ የሆነው ሥቃይ፣ ሐዘን ልቅሶና ሞት ሁሉ ታየው። በየዘመኑ የኖረውና በየቦታው ተበታትኖ የሚገኘው የሰው ዘር ሕመም፤ በልቡ ውጋት ሆነበት።" (የዘመናት ምኞት ገጽ. 221- 552)

በመጠኑ የምናውቃቸው ወይም በጣም ቀረቤታ ያለን ወገኖች ላይ ደርሶ የተመለከትነውን ልብ የሚሰብር ሐዘን ቆም ብለን ማሰብ እንችላለን። በተጨማሪ በየዕለቱ በመገናኛ ብዙሃን የምንሰማቸውንና የምናያቸውን አሳዛኝ አደጋዎችና ልብ የሚሰብሩ ትዕይንቶች አክለን ለመመልከት እንሞክር። ይህ ሁሉ ሲሆን ነገሮችን እኛ ከምናይበት አቅጣጫ ሳይሆን በጥልቅ ማስተዋል የሚመለከተውና የሚገነዘበው ጌታ በመላው ሰብዓዊው ፍጡር ላይ የደረሰው ዋይታ ያስለቅሰዋል።

የሳልቬሽን አርሚ መስራቹ ጀነራል ዊልያም ቡት እንዲህ ሲሉ ተናግረው ነበር " 'በአንድ ከተማ ላይ በሚደርስ ውድመት ሐዘኔታ የማይሰማህ ከሆነ ልንጠቀምብህ አንችልም' " –Roger S. Greenway and Timothy M. Monsma, Cities: Missions' News Frontier (Grand Rapids, Mich.: Baker Pub. Group, 2000) p. 246. እነዚህ ቃላት ለእያንዳንዳችን ምን ይሉናል?

# ሌላው አጽናኝ

“የርኅራኄ አባት፣ የመጽናናትም ሁሉ አምላክ የሆነው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ። እኛ ራሳችን ከእግዚአብሔር በተቀበልነው መጽናናት፣ በመከራ ያሉትን ማጽናናት እንድንችል፣ እርሱ በመከራችን ሁሉ ያጽናናናል ” (2ቆሮ. 1:3-4)። ጳውሎስ--በእኛ ላይ የሚደርሰው መከራ ለሌሎች ርኅራኄ እንድናደርግና እንድናጽናናቸው ይረዳናል ሲል ምን ማለቱ ነው? የእነዚህን ቃላት ተጨባጭነት በራስዎ ሕይወት ተለማምደው ከሆነ ተሞክሮዎ ምን ይመስላል?

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

በሥቃያችን ከክርስቶስ የምናገኘውን መጽናናት ወደ ሌሎች ማስተላለፍ እንችላለን። በእኛ ላይ ከደረሰው ሐዘን የምንቀስመው ትምህርት ለሌሎች ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠት ያስችለናል። በአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያኖች መጽናናትን በሚሹና በሚያጽናኑ አባላት የተሞላች ናት። ይህ ስብጥር ቤተ ክርስቲያንዎን አስተማማኝ የአምልኮና “የመማጸኛ ከተማ” (ዘኍ. 35) እንዲሁም ወደ ማኅበረሰቡ የሚፈስ የፈውስ ወንዝ (ሕዝ. 47፡1- 12) ያደርጋታል። ሐዘኔታና ርኅራኄ ማሳየት ራሱን የቻለ ክህሎት ነው። በመቀጠል የቀረቡት ጥቂት ነጥቦች ይህንኑ ያሳያሉ። ሐቀኛ መሆን፡--ከሚናገሩት በላይ ያዳምጡ። በፊትዎ የሚነበበውና በአካልዎ የሚታየው ሁኔታ ለሌሎች ለሚያሳዩት ሐዘኔታና ማጽናናት ኃይል ስለ መሆኑ እርግጠኛ ይሁኑ።

ከግል ስብዕናዎ ወጣ ያለ ርኅራኄ ያሳዩ፡--አንዳንድ ሰዎች ልብ በሚሰብር ሁኔታ ውስጥ ካለው ሰው ጋር አብረው በማልቀስ የተሰማቸውን ሐዘን ይገልጻሉ። ሌሎች ግን ከዐይኖቻቸው እንባ ጠብ ባይልም ሐዘን ለተቀመጠው መጽናናት ሊያመጣ የሚችል ነገር ያስተባብራሉ።

በሐዘኑ ላይ መገኘት ከማውራትና አንዳንድ ነገሮች ከማድረግ በበለጠ ተጎጂውን ያጽናናል። ሰዎች ሐዘናቸውን በፈለጉበት መንገድ እንዲገልጹ ይተዉአቸው እንጂ ተጽእኖ አያድርጉባቸው።

ሰዎች በተለምዶ ሐዘናቸውን ከሚገልጹባቸው አካሄዶች ጋር ትውውቅ ይኑርዎት። “ምን ያህል እንዳዘኑ ይገባኛል” የሚለውን አባባል ላለመጠቀም ጥንቃቄ ያድርጉ። የባለሙያ

የምክር አገልግሎት ማግኘት የሚቻልበት መንገድ ይኖራል። ከልብዎና ለማድረግ እርግጠኛ ካልሆኑ በቀር “በጸሎት አስብሃለሁ/ አስብሻለሁ” አይበሉ። ሁናቴዎች ምቹ

ሲሆንልዎ በሐዘን ላይ ያለውን ሰው በቂ ጊዜ ወስደው ይጎብኙ። አጽናኝ የመጽሐፍ ቅዱስ ተስፋዎችንም ያካፍሉ። የጉብኝት ቡድን በቤተ ክርስቲያንዎ ወይም በማኅበረሰብዎ

መሃል ያደራጁ።

## ተጨማሪ ሀሳብ

የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ዘዳ. 24:10—22፣ ዮናስ 3፣ ሚልክ. 3:17፣ ማቴ. 15:32—38፣ ማር. 6:34—44፣ ገላ. 6:2፣ ዕብ. 10:32— 34፡፡ Read Ellen G. White, “Be Sympathetic to All Men,” p. 189, and “Thoughtful of Others,” p. 193, in My Life Today; “The Privilege of Prayer,” p. 100, in Steps to Christ; “This Is Pure Religion” and “The Parable of the Good Samaritan,” chapters 4 and 5, in Welfare Minis- try.

ጊዜው የአመት በዓል ምሽት ነው፡፡ ጥቂት ቤተሰቦች ምግብና መጠነኛ ቁሳቁሶች አዘጋጅተው ከሚያማምሩ ትናንሽ ልጆቻቸው ጋር የከተማቸውን ቤት ዐልባ የጎዳና ላይ ነዋሪዎች ለመመገብ ወደዚያው አመሩ፡፡ በከተማው የተለያዩ አቅጣጫዎች በማምራት በግማሽ ሰዓት ውስጥ ያሰቡትን አከናውነው ጨረሱ፡፡ ታዲያ ወደ አቆሟቸው መኪናዎቻቸው እየተለመሱ ከመሃላቸው አንደኛው “ይህን በማድረጋችን ደስ ብሎኛል፡፡ ግን እራት ካበላናቸው ሰዎች አብዛኞቹ በአሁኗ ደቂቃ እንደገና ሊርባቸው እንደሚችል አስተውላችኋል?” ሲል ጠየቀ፡፡ የእኛን ማጽናናት፣ ርኅራኄና እርዳታ የሚሹ--ከነውስብስብ ችግሮቻቸው ጋር ጎዳና የወጡ አስደንጋጭ ቁጥር ያላቸው ሕዝቦች ከመኖራቸው አኳያ--አንድ ሰው እነዚህን ምስኪኖች ከተረጂነት ማውጣት--አባይን በጭልፋ እንደ ማለት ነው ብሎ ሊናገር ይችላል፡፡ ሆኖም በመጀመሪያ ደረጃ መገንዘብ ያለብን፤ እንደዚያ ካሰብን ማንም--ማንንም መርዳት ስለማይችል ሁኔታው እየተባባሰ እንጂ እየተሻሻለ አይሄድም፡፡

በሌላ በኩል--ሌሎችን የመርዳት አቅም ያለው እያንዳንዱ ሰው ሌላውን ቢደግፍ፤ ዛሬ ከፍተው የምናያቸው ዕጦቶች ያን ያህል የተባባሱ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ በሁለተኛ ደረጃ መገንዘብ ያለብን--ሰብዓዊው ሥቃይና እንግልትም ሆነ የክፉው ተግባር ከምድር እንደሚጠፉ መጽሐፍ ቅዱስ ተስፋ አይሰጠንም፡፡ ይልቁንም በተቃራኒው ነው የተነገረን፡፡ የሱስ በምድር ይመላለስ በነበረበት ወቅት ሰብዓዊውን ሥቃይ ወደ ፍጻሜ አላመጣም፡፡ ሆኖም ማድረግ ይችል የነበረውን ሁሉ አድርጎአል፡፡ እኛም የእርሱን ዱካ ተከትለን የእኛን ማጽናናት፣ ርኅራኄና እርዳታ ለሚሹ ሁሉ እንድናበረክት ተጠርተናል፡፡

## የመወያያ ጥያቄዎች:

1. ቤተ ክርስቲያንዎ ልባቸው ለተሰበረ አስተማማኝ የፈውስ ቦታ መሆን የምትችለው እንዴት ነው?

2. በሚከተለው በትምህርተ ጥቅስ የተቀመጠ ሀሳብ ላይ ተወያዩ “ብዙዎች እግዚአብሔር ለምን ጣልቃ ገብቶ አንድ ነገር አያደርግም ብለው አጥብቀው ሲገረሙ፤ እግዚአብሔር ደግሞ እነዚህ ሁሉ ሕዝቦቹ በችግር ላሉ ወገኖች ስለ ምን ግድ እንደማይላቸው ይገረማል”–Dwight Nel- son, Pursuing the Passion of Jesus (Nampa, Idaho: Pacific Press Publishing Association, 2005). በቀረበው ተግዳሮት ነክ ጽንሰ ሀሳብ ላይ ይስማማሉ? እንዲያ ከሆነ ይህን ለመለወጥ ምን ማድረግ እንችላለን?

3. “እንደው እንደ ዘበት የምንናገራቸው ደግ ቃላትና የምንሰጣቸው አነስተኛ ትኩረቶች በሰብዓዊው ነፍስ ላይ የከበደውን የፈተናና የጥርጣሬ ደመና ይበትናሉ። ያለ አንዳች መመጻደቅ በእውነተኛ ልብ የሚገለጽ የክርስቶስ ዓይነት ርኅራኄ የልቦችን በር የመክፈት ኃይል አለው።”–Ellen G. White, Testimonies for the Church, vol. 9, p. 30. ደግነትና ርኅራኄ በሐዘን ወደ ተሰበረው ልብ ጠልቆ በመግባት ስለሚያመጣው መጽናናት የሚነግረን ይህ መልእክት--መልካምነት ስላለው አስደናቂ ኃይል ምን ይለናል?